# ማ ማ   በ ሰ ማ ይ

ማማ በሰማይ በሕይወት ተፈራ በ2007 ዓ.ም. በአማርኛ በጌታነህ አንተነህ ተተርጉሞ ለማንበብ በቅቻለሁ።አንዳንድ የተሰሙኝን ስሜቶች በማቅረብ ተሳትፎ ለማድረግ ብዬ ነው።

„ማማ በሰማይ የፍቅር ታሪክ ነው።የአብዮትም፣ የተስፋም፣ የሕልምም፣ የአመጽም፣ የሽብርም፣ የመተማመንም፣ የመከዳዳትም፣ የሰቆቃም፣ የሰቀቀንም፣ እራስን በራስ የመለወጥም፣ የድል አድራጊነትም፣ የነዚህ ሁሉ ሰብዓዊ ረቂቅ ባሕርያት ታሪክ ነው።መጽሐፉ፣ ደም የጠማው ወታደራዊ ጁንታ ባቀጣጠለው ታይቶ የማይታወቅ ቁጥር ያለው ሕዝብ -በተለይ ወጣቱ - እንደ ቅጠል የረገፈበት የኢትዮጵያ ታሪክ አንድ ወቅት ቅልብጭ ያለ ስዕል ነው።በታሪክ ውስጥ ብቅ ብለው ከጠፉት እጅግ ጨካኝ አምባገነን ስርዓቶች አንዱ በሆነው ላይ በመነሳሳትና በቁርጠኝነት በመጋፈጥ ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለማህበራዊ ፍትሐና ለሰብዓዊ ክብር የታገሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታሪክም ነው።" የሚለው በመጽሐፉ ጀርባ ላይ ታትሞ የመጽሓፉን ጭማቂ የሚመስል ይዘት ቀልበጭ ባለ መልኩ ቀርቧል።

„መጽሓፉ በአንድ የታሪክ ወቅት በየትኛውም ድርጀት ዙሪያ ተሰልፎ እንደ ንጋት ጮራ ፍንጥቅ ብሎ የጠፋው የዛ ታጋይ፣ ህልመኛና ታላቅ መስዋዕትነትን የከፈለው ትውልድ ታሪክ ነው።ታወር ኢን ዘ ስካይ ጭቆናናን ግፍን ተቃውሞ በምትኩ ፍትህን፣ ነጻነትን፣ እኩልነትንና የሰውን ልጅ የማይገሰስና የማይደፈር ክቡርነት እውን ለማድረግ የተነሳውና በሕይወቱ ሆነ በሌላ የከፈለው የዛ ራዕይ ይዞ የተነሳው ወርቃማው ትውልድ ውደሳ፣ ሙገሳ ወይም ሰለብሬሽን ነው።" በሚል መልኩ በምስጋና ስር በገጽ 5ና 6 ደራሲዋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የእሸቱ ጮሌ ሕንጻ ሰኔ 1 ቀን 2005 ዓ.ም. በመጽሃፉ ምረቃ ላይ ባቀረበችው ጽሁፍ ተዘግቧል።

በመጽሐፉ ውስጥ አንዳንድ የረሳኋቸውን ቃላት እንደገና እንዳስታውስ አድርጎኛል ለምሳሌ ጮካ፣ ሪቮ፣ ሳቡተርስ፣ መሬት ለአራሹ፣ ትምህርት ለሁሉም ይዳረስ፣ ዴሞክራሲ መብቶች አሁኑኑ፣ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፣ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር፣ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ይቀነስ፣ ፊውዳሊዝም ይውደም፣ ኢምፔሪያሊዝም ይውደም፣. . . ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

ስለ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ስለነበረው ሁኔታ ስለ ሴቶች ማደሪያ ቤቶች፣ ስለ ኪኔዲ ላይበረሪ፣ ስለ ኪስንግ ፑል፣ ስለ ተማሪዎች ምግብ ቤት፣ ስለ ሚኒስከርት፣ . . . ወዘተ በጥሩና ዘርዘር ባለ መልኩ ቀርቧል።ግዜው የአብዮት ግዜ ስለነበረ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከፍተኛ እንቅሰቃሴ ያደረጉበት ወቅት መሆኑንም በመጽሐፉ ውስጥ በተገቢው ተተርኳል።በአጠቃላይ የተማሪዎች እንቅስቃሴ አፓርታይድን፣ ጽዮናዊነትን፣ በቪዬትናም የሚደረገውን ጦርነት በመቃወም፣አንዲሁም በአሚሪካ ውስጥ የተቀጣጠለውን የሰብዓዊ መብቶች ትግልና በአፍሪካና በላቲን አሜሪካን የተፋፋሙትን የአርነት እንቅስቃሴዎች በመደገፍ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ታትቷል።

## መንግስተ ሰማያትን ወደ ምድር!

„አዲሱ ርዕየተ ዓለም ለማህበራዊ፣ ለኢኮኖሚያዊም ሆነ ለፖለቲካዊ ደዌ ሁሉ መፈወሻ ፍቱን መድሃኒት ተደርጎ ተወሰደ።መንግስተ ሰማያትን ወደ ምድር የሚያወርድ ሆኖ ቀረበ፣ እናም ተማሪዎቹ በተምኔታዊ ርዕዩት ማልለው ወደሀገራቸው ሊያግዙት ቋመጡ።“(76) ከጸሃፊዋ ጋር ስለመንግስተ ሰማያት ያቀረበቸው ፈጽሞ ከሁኔታው ጋር የማይጣጣምና ያው ግራውን አይዲዮሎጂ ለመቀጥቀጥና ሊሰራ እንደማይችል አድርጎ ለማቅረብ በማሰብ ካልሆነ በስተቀር፣ ይህ አይዲዮሎጂ ነበረ፣ ዛሬም አለ። ነገም ይኖራል። በዚያን ግዜ የነበረውም አማራጭ የግራው

አይዲዮሎጂ ነበር። ሌላውማ ሕዝብን መቦጥቦጫ አይዲዮሎጂ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይጠቅም ህዝቡ ተረድቶ በቃኝ አንገፈገፈኝ ብሎ አንቅሮ ተፍቶታል።ይህ ማለት ግን እንደ ካፒታሊዝም አይዲዮሎጂ፣ የግራው አይዲዮሎጂ ምንም የማይወጣለት አይደለም ወይም የሚተቸብት ነገር የለውም ማለት አይደለም።ጸሃፊዋ በዚያን ወቅጥ አማራጭ ነው የምትለውን አላቀረበችም።

## ለምዕራባዊው ዓለም ጥላቻ!

„ተማሪዎቹ ለምዕራባዊው ዓለም ክፉ ጥላቻ እድሮባቸው ስለነበር፣ ምዕራባዊ የሆነ ነገር ሁሉ ደማቸውን አፈላው።መጋቢት 1960 ዓ.ም. ላይ አንዳንድ ሴት ተማሪዎች የፋሽን ትርዒት ባዘጋጁ ግዜ፣ ተማሪዎቹ በተጋባዥ እንግዶቹ ላይ እንቁላል በመወርወር ትርዒቱን አዳናቀፉባቸው።ፖሊስ አስለቃሽ ጋዝ ተኮሰባቸው።ብዙ ተማሪዎችም ታሰሩ።“(77)ምዕራባዊ የሆነ ነገር ሁሉ የሚለውም ለማጋነን ካለሆነ በስተቀር የፋሺን ዝግጅቱን መቃወማቸውን መጥቀሱ በቂ ነበር።በእኔ እምነት ዛሬም ያንን ተቃውሞ መደረጉ ትክክል ነው ብዬ አምናለሁ።

የጸሃፊዋ በተለይ የኢሕአፓን አሰራር አስመልክቶ በተለያዩ ሁኔታዎች የነበሩትን ሁኔታዎች በመግለጽ፣ እሷ በምትረዳው ደረጃ አስቀምጣለች። ትንሽ ዘርዘር ባለ መልኩ እንድታቀርብ ምኞቴም ቢሆን፣ ይህንንም ደፍራ ወጥታ በማቅረቧ በብኩሌ ጎሽ ጎበዝ እላታለሁ።ይህን ስል በጻፈቸው ሁሉ እስማማለሁ ማለት አይደለም። ድርጅቱ አስካዛሬ አንድ መጽሓፍ ለመጻፍ ሳይችል በመቅረቱ ከሚያዝኑት ሰዎች አንዱ ነኝ። ይጻፋል ብዬም ተስፋ አላደርግም። ብዙዎቹ በሕይውት የሉም።ከዚህ አንጻር እንደ አንድ ግለስብ ይህ መጽሓፍ መጻፉ እስየው የሚያሰኝ ነው።

„አዲስ አበባ በአራት ቀጣናዎች ተከፍላ እንደነበር፣ ቀጣና አንድ መርካቶን፣ ጉለሌን፣ ተክለሃይማኖትን . . . ወዘተ፣ ቀጣና ሁለት ነፋስ ስልክን፣ ቄራን፣ . . . ወዘተ፣ ቀጣና ሶስት አራት ኪሎን፣ ስድስት ኪሎን፣

እንጦጦን፣ . . . ወዘተ እንደሚያጠቃልል በመጽሃፉ ውስጥ ተገልጿል። የወጣቱ ክንፍ በሶቭዬት የወጣት ኮምዩኒስት ፓርቲ አምሳያ የተዋቀረ እንደነበር ነው።የራሱ የሆነ ከፊል ነጻነት እንደነበረው፣ ድርጅታዊ መዋቅሩ ከፓርቲው መዋቅር ጋር በተዋረድ ይሄድ እንደነበር ነው።(125)

„ከምልመላው ጥድፊያ ምክንያቶች አንዱ ተቀናቃኙን መኢሶንን ለመቅደም ነበር። ኢሐአፓ ክፉ ቅጽል እየሰጠ ከወጣቱ ለማራቅ ሞክሯል።“(126) „ክፉ ቅጽል“ የምትላቸውን ስላልጠቀሰች ብዙም ማለት አይቻልም።የመኢሶን ካድሬዎች በአሰሳዎቹ ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ሰው በማስፈጀታቸውና ለደርግ በማጎብጎባቸው „ባንዳ“ ይባሉ እንደነበረ አስታውሳለሁ።ይሄ ቅጽል ክፉ ነበር ወይ ለሚለው አዎ ክፉ ነበር። ድርጊታቸውም በባንዳነት በማደራቸው ብዙ ህይወት እንዲቀጽፍ አስደርገዋል። ይሄ በተጨባጭ የሆነና ያደረጉት ነው።ሌላው የምልመላ ጥድፊያው መኢሶንን ለመቅደም እንደነበር ተጠቅሷል። ማንኛውም ድርጅት ብዙ አባላት ለማፍራት መንቀሳቀሱ የነበርና ዛሬም ያለ ነው። እኔ መኢሶንን በተለይ ለመቅደም የተሰራ ከሆነና ከተቻለ ችግሩ ምኑ ላይ እንደሆነ ለእኔ አልታየኝም።

„አባላቱ ከብረት የጠነከረ ስነ-ስርዓት እንዲኖራቸው ይጠበቃል።የወጣቱ ክንፍ እንደፓርቲው ሁሉ የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን መርሕ ይከተላል።ግለሰቦች ለወጣቱ ክንፍ፣ ንዑሳን ደግሞ ለብዙሃኑ እንደሚገዙ ተምረናል።“(127)ይሄ ትክክል ነው።

በወጣቱ ክንፍ ለ10 ወር የሰራ የፓርቲው አባል መሆን ይችል እንደነበርና የወጣት ፋና ወጊ በመባል የሚታወቅ እድሜያቸው ከ11 አስከ 14 ዓመት የነበሩ በድርጅቱ ስር ይታቀፉ እንድነበርም ተገልጿል።ይሄ ለእኔ አዲስ መረጃ በመሆኑ መረጃውን በማግኘቴ ጸሃፊዋን ላመሰግን እወዳለሁ።

## ግዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት!

ግዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ታክቲካዊ መፈክር መሆኑ ትክክል ነው። ግን ግዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት በዚያን ግዜ ተግባራዊ ሊሆን ቢችል ሁኔታው ሌላ መልክ ሊይዝና የመንግስቱ ሃይለ ማርያም ስልጣኑን የመቆጣጠር ሁኔታ ሊቀይረው ይችል ነበር ብዬ አምናለሁ። በግዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ጥያቄ በወቅቱ በኢሕአፓ በኩል መቅረቡ ትክክል ነው።ሌላው ከዚሁ ጋር አብሮ የሚያያዘው የከተማ ትጥቅ ትግል ድርጅቱ በቋሚነት የመንግስት ስልጣን ለመያዝ እንዳወጀ ተደርጎ የሚቀርበው አቀራረብ ፈጽሞ ትክክል አይደለም። የመኢሶን ካድሬዎችና የደርግ የግድያ ላይሳንስ የተሰጣቸው ገዳዮች የኢሕአፓ ነው የሚሉትን ሰው ሁሉ እያሳደዱ በሚገድሉበት ወቅት በተወሰነ ደረጃ ራሱን ለመከላከል በተወሰኑ የመኤሶን ካድሬዎችና መሪዎች ላይ እንዲሁም የቀበሌ ገዳዮች ላይ እርምጃ መወሰዱ ለተወሰነ ግዜም ቢሆን የተወሰኑ ሰዎችን አድኗል። በኋላ ግን በጣም ተለጥጦ በኢሕአወሊ በኩል አንዳንድ የተወሰዱ እርምጃዎች የተሳሳቱ እንደነበሩ ተነግሯል።በወቅቱ በአንድ ሰው ላይ ኢሕአፓ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ሰውየው ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ሶስት ግዜ በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ማስጠንቀቂያውንም አልቀበልም ብሎ በድርጊቱ ከቀጠለ ድርጅቱ እርምጃ ይወስድ ነበር።

## የግድያ ሙከራ!

በመንግስቱ ሃይለ ማርያም ላይ የግድያ ሙከራ መስከረም 13 ቀን 1969 ዓ.ም መደረጉ በሬዲዬ ይፋ ሲሆን ጸሃፊዋ በጣም ከእግር አስከ ራሷ በፓርቲው ተግባር በጣም እንደሰቀጠጣት ገልጻለች።ከዚያ በፊትስ በደርግና በመኢሶን ካድሬዎች አቀናጅነት የተገደሉትስ የኢሕአፓ አባላት?።በበኩሌ መንግስቱ ሃይለ ማርያም ቢገደል ኖሮ በደርግ ውስጥ ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል አምናለሁ። መንግስቱ ሃይለ ማርያም የፈጃቸው እነ ጀነራል ተፈሪ ባንቲና ሻምበል ዓለማየሁ ሞገስ መንግስቱን በመናቅ የእልቂቱ ሰለባ ባይሆኑ ኖሮ፣ ለውጥ ሊመጣ ይችል እንደነበር

የእኔ እምነት ነው። ስለሆነም በመንግስቱ ሃይለ ማርያም መገደል የማዝን፣ የሚሰቀጥጠኝና ትክክል አይደለም ብዬ የምከራከር ሰው አይደለሁም።በእኔ ግንዛቤ መሰረት ደርግ በኢሕአፓ ላይ መስከረም 1969 ዓ.ም. የመደምሰስ አዋጅ ካወጀ ከ23 ቀናት በኋላ ኢሕአፓ በመንግስቱ ላይ የግድያ ሙከራ እንዳደረገ ነበር።

ደርግ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. የመንግስት ስልጣን እንደያዘ አንድ አዋጅ ማወጁ እውነት ነው። በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ውስጥ „ይህ አዋጅ ስራ ላይ እስከዋለበት ጊዜ ደረስ የ“ኢትዮጵያ ትቅደም“ ፍልስፍና መቃወም፣ የስራ አድማ ማድረግ፣ ያልተፈቀደ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም የሕዝብን ሰላምና ጸጥታ ሊያናጋ በሚችል አድራጎት ውስጥ መገኘት የተከለከለ ነው።“ ሲል በአንቀጽ 9 ደግሞ „በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንቀጽ 8 የተዘረዘሩትን ትእዛዝ የሚጥሱትን ለመዳኘት ልዩ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ይቋቋማል. . . በእነዚህ ልዩ ፍርድ ቤቶች የተላለፉ የፍርድ ውሳኔዎች ይግባኝ አይጠየቅባቸውም።“ የሚል ነው። እነዚህ ሁለት አንቀጾች የሚገልጹት ደርግ ወደ ካምፕ እንደማይመለስና ሕዝቡን ጸጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት የወሰነበት ሁኔታ ነበር።

ከዚያም ደርግ ያለምንም ፍርድ ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. 59 ሰዎች ገድሏል።

## የ“ሀ“ ና „ለ“ ጉዳይ!

„ሀ“ ና „ለ“ ከፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ስለመባረራቸው ጸሐፊዋ ፓርቲው እንደዚህ ዓይነት ነገር ያደርጋል ብላ ለማመን እንደተቸገረች ገልጻለች። ግን ለምን? አንድ ፓርቲ ለድርጅቱ ዓላማ ጠቃሚ ያልሆኑ ወይም አደገኛ የሆኑ አባላትን ከድርጅቱ ማስወገድ ግልጽ ሊሆን ይገባል።ዋናው ቁምነገር የድርጅቱን ሕገ-ደንብ ተከትለው የሚሰሩ አመራሮች ሊሆኑ ይገባል።

ሁለት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የተገለሉት በስነ-ስርዓት ምክንያት እንደሆነ ተገልጿል። ጸሃፊዋ የሁለቱም አድናቂ ናት።ይሄ መብቷ ቢሆንም በእኔ እምነት „በነሱ ደረጃ ያሉ ጓዶችን ለማየት በመታደሌ“ የሚለው እኔ አልተመቸኝም።ለመካብ የተደረገ መንደርደር ነው ብዬ ስላመንኩ ነው።ሁለቱ ግለሰቦች በኋላ „አንጃኞች“ እንደተባሉና ሁኔታው እየከፋ እንደመጣም አልሸሸገችም።

አንጃኞቹ በሌሎች የኢሕአፓ አባላት ላይ ያደረሱትን ጉዳት በተገቢው ለመግለጽ የተፈለገ አይመስለኝም።ለብዙ ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆኑ አንጃኞች መኖራቸውን መካድ አይቻልም። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ከሜይ ዴይ በዓል አንድ ቀን በፊት በተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ለደርግ ኢንፎርሜሽኑን አሾልከው በመስጠት ደርግ ተዘጋጅቶ ብዙ የኢሐአፓን አባላትና ደጋፊዎች ለመገደላቸው አንጃዎች ምክንያት ነበሩ።ሌሎችም ብዙ ሊባሉ የሚችሉ ነጥቦች አሉ። እዚህ ላይ ጸሐፊዋ በሌላ ወገን ሆና የፍቅሩም ሁኔታ ተጽዕኖ አድርጎባት የአንዱን ወገን ብቻ አቅርባለች።

ግልጽ ማድረግ የምፈልገው ጌታቸው ማሩ መገደሉ በምንም መልክ የምደግፈው ነገር አይደለም። የማልስማማው ድርጅቱ ትእዛዝ ሰጥቶ እንዳስገደለው ለማድረግ የቀረበውን አቀራረብ ለእኔ ስህተት ነው።ምክንያቱም ጌታቸው ጠባቂውን በካራቴ መቶ ለማምለጥ ሲሞክር እንደተገደለ ነው።ሁላችንም የምንሰማው አሉ አሉ እንጂ በቦታው አልነበርንም።ጠባቂው ከሚገድለው ይልቅ በቁጥጥር ስር ቢያደርገው የተሻለ ነበር ግን አልሆነም።

የዴሞክራሲያዊ አሰራርን መከተል ግድ ስለሆነ ጌታቸውም ሆነ ብርሃነ መስቀል ይህንን ማክበር ነበረባቸው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ እነርሱ በድርጅቱ ውስጥ ሌላ ድርጅት በመፍጠር ለመንቀሳቀስ ሞክረዋል። ይሄ ትክክል አልነበረም።

„ጥር 25 ቀን 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አብዮት በአስፈሪ ሁኔታ ወደ ጨለማውና ወደአረመኔነት የዞረበት ቀን ነው።“(192)የሚለውን አባባል መንግስቱ ሃይለ ማርያም ሌሎቹን አዘናግቶ በመረሸን የብቸኛ መሪነቱን ያረጋገጠበት ሁኔታ ነበር። ይህ በሌላው ግሩፕ ፍላጎት አቅጣጫ ቢጓዝና መንግስቱን ቁጥጥር ስር ማድረግ ቢቻል አዎንታዊ የሆነ አቅጣጫ ሊፈጠር ይችል ነበር የሚል ግምት ነበረኝ።መኤሶንንም አደብ ግዛ ተብሎ በአሰሳውና በቀይ ሽብር ዘመቻ ወቅት ከነበረው ሚና እንዳይገባ ማድረግ ይቻል ነበር። ግን አልሆነም።

## የኢሕአፓ የመጀመሪያዋ ጥይት

„ቀደም ሲል የኢሕአፓ ጥይት ዒላማ የነበረው መኢሶን ለበቀል ተነሳ።“(194) የሚለው ኢሕአፓ ቀድሞ መኢሶን ላይ ጥይት እንደተኮሰ ለማድረግ የሚቀርብ አባባል ነው። እውነቱ ግን እንደዚያ አልነበረም።መኢሶን ከደርግ ጋር በመቆራኘት የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ካድሬዎችን በማስልጠን፣ ቀበሌዎችን በመቆጣጠር፣ በአዲስ አበባ ከተማ አሰሳዎችን በማድረግ፣ የመግደል ላይሳንስ የተሰጣቸውን ገዳዮች ደርግ እንዲያሰማራ በማድረግ፣. . . ወዘተ ብዙ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች እንዲገደሉ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።ኢሕአፓ መኢሶን ላይ የመጀመሪያውን ጥይት አልተኮሰም።የፍቅሬ መርዕድ ግድያ ራሱ የተካሄደው መስከረም 1969 ዓ.ም. ደርግ በኢሕአፓ ላይ የማጥፋት ዘመቻ አዋጅ ካወጀ በኋላ ኦክቶበር 2 ቀን 1969 ዓ.ም. ነበር።መንግስቱ ላይም የተደረገው ሙከራ በኢሕአፓ ላይ የማጥፋት ዘመቻው ከታወጀ በኋላ ስፕቴምበር 23 ቀን ነበር።

## አንጃዎች!

አንጃዎችን በተመለከተ በጣም የአንድ ወገን አስተሳሰብን ብቻ በማጉላት፣ በድርጅቱ ወገን የተሰጠውን እውነታ የማይገልጹ ሁኔታዎች ተዘግበዋል።

„አብዛኞቹ „የሚያውቁት“ ወይም የተነገራቸው ነገር ቢኖር፣ አንጃዎቹ ከደርግ ጋር ለመቀላቀል ፈልገዋል፣ ፓርቲውን ሊበታትኑ ይፈልጋሉ፣ የፓርቲውን አባላትም ለጠላት እያጋለጡ ይሰጣሉ የሚባለውን ነበር።“(215) የሚለው በተወሰነ ደረጃ እውነት ነበር። ከደርግ ጋር ለመስራት ፍላጎት ነበራቸው።ፓርቲውንም ለማዳከም በሚገባ ተንቀሳቅሰዋል።ብዙም የኢሕአፓን አባላት ለደርግ በማጋለጥ አስገድለዋል።እነዚህ ያፈጠጡ እውነቶች ናቸው።ጸሐፊዋ ግን የድርጅቱ አብዛኞቹ አባላት የተነገራቸውን እንዴት ማወቅ እንደምትችል አይገባኝም።ምክንያቱም ድርጀቱ ህቡዕ የሚንቀሳቀስና አንድ አባል ሌሎቹ የሚያውቁትን ለማወቅ የሚችልበት መንገድ አልነበረምና።

„ይኸ ሁሉንም ጥፋት በአንጃዎቹ ላይ የማላከክ ተግባር ዓላማ ነበረው።እሱም፣ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካላት የፈጸሚቸው ስህተቶች የአንጃዎቹ ጥፋት መስለው እንዲታዩ ማድረግ ነበር።ለመኢሶን ከነበረ ጥላቻ ይበልጥ ለአንጃዎች የነበረ ጥላቻ በፓርቲው ውስጥ የአንድነት መገለጫ ሆነ።“(216) የሚለው አባባል ኢሕአፓ እንደ ድርጅት ጥፋት ናቸው ያላቸውን በግልጽ በጽሁፍ በተፈላጊው ግዜ አውጥቷል። ነገር ግን ድርጅቱ ላጠፋው ጥፋት ሁሉ አንጃዎችን ተጠያቂ አላደረገም። አንጃዎቹ ተጠያቂ በነበሩበት ብቻ ተጠያቂነታቸውን ገልጿል።ለአንጃዎች የነበረ ጥላቻ ከመኤሶን ይበልጥ ቢሆንም የሚገርም አይሆንም።ምክንያቱም የድርጅቱ አባላት የነበሩ በድርጅቱ ላይ መኢሶን ይሰራቸው ከነበሩት የማይለዩ ስራዎችን በመስራታቸው ነበር።ይህ ግን በኢሕአፓ ውስጥ የአንድነት መግለጫ ሊሆን አይችልም። የአንድነት መግለጫው የድርጅቱ ዓላማዎች ብቻ ናቸው።

„ተስፋ ተቀጨ።ደስታና ፈንጠዝያ ወደተስፋ መቁረጥ ተቀየረ።በነዚያ አብዮታዊ ቀና በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ተዘርግቶ የነበረው ቀስተ ደመና ጥቅልል ብሎ ተነሳ።“(253) የሚለው በዚያን ወቅት የነበረውን ሁኔታ በጥሩና ቀልበጭ ባለ መልኩ ቀርቧል።

„የአብዮቱ በጥባጭ ልጅ“ መኢሶን ነሐሴ 1969 ዓ.ም. ላይ ከደርግ ጋር ፍቅሩ አበቃለትና ህቡዕ ገባ።“ (254) በኋላም የመኢሶን አባላት በመረሸን ደርግ ካስወገደ በኋላ ወደወዝ ሊግና ወደማሌሪድ በማዞር ፈጅቷቸዋል። ይህ የሚያሳየው መንግስቱ ሃይለ ማርያም ስልጣኑን ለማንም እንደማያስቀምስና ለሕዝብ የማስረከብ ፍላጎት ፍጹም እንዳልነበረው ነው። እንጂ የግድያ ሙከራ ኢሕአፓ ስላካሄደበትም አልነበረም።

## ያ ትውልድ!

„ለአሳዛኝ አፈጻጸም የተዳረጉ ጀግኖች፣ ስህተቶቻቸው እንዳሉ ሆነው፣ ‘ወርቃማው ትውልድ‘ ናቸው፣ ‘ይሉኝታ የማይበገረው‘ የሩቅ ህልም ያለመ፣ ታላቅ ራዕይ የነበረው፣ ህይወቱን ለሌላው አሳልፎ የሰጠ ትውልድ።ለእኩልነት፣ ለነጻነት ለማህበራዊ ፍትህ እና ለሰብዓዊ ክብር ሲሉ ገድለዋል፣ ሞተዋል።ኢትዮጵያ መስዋዕትነታቸውንና ታላቅ ርዕያቸውን በሚያነቡ ዓይኖች ምንጊዜም ስታስታውስ፣ የፈጸሙትን ስህተት ደግሞ በይቅር ዓይነት ትዘክረዋለች። እግዞኦ! በቅጽበት ልጆቿን ተነጥቃ የወላድ መካን ሆነች።“(254-255)የሚለው አቀራረብ እጅግ በጣም ድንቅ አቀራረብ ነው።በበኩሌ ምንም የምጨምረው ወይም የምቀንሰው ነገር የለኘም።

## ከደርግ ማሰቃያ ዘዴዎቹ አንዱ፣

የደርግ የማሰቃያ ዘዴዎቹ ከሆኑት አንዱን ዓይነት ጸሃፊዋ በሚከተለው መልኩ ለአንባቢያን በማቅረቧ፣ በዚህ ሁኔታ ላላፉት ሰዎች ሁሉ ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ነው።“ምርመራ ቤቱ የሰው ልጅ ምናብ ሊደርስ

በቻለበት ጥበብ በተሰሩት የማሰቃያ ቁሳቁስ ተሞልቷል።ጨለምለም ያለ ነው። ጠና ያለው ደህንነትና አንድ ካድሬ ሆነው ሐኪሙን ከእንጨት በተሰራ መስቀያ ላይ እያንጠለጠሉት ነበር።ዓይኖቹን በጨርቅ ሸፈኗቸው፣አፉንም ወተፉት።ከዚያ የሚወናጨፍ ዱላ የውስጥ እግሮቹን በሃይል ሲጠበጥባቸው ታየኝ።አልፎ-አልፎ የደህንነት አባሉ ቆም እያለ ቡትቶውን ከአፉ ያወጣለትና እውነቷን እንዲያወጣ ያዘዋል።ዝግጉን ሲያደርገኝ፣ ዓይኖቼን ጨፈንኳቸው።የተጠራሁት ያንን እንዳይ መሆኑን ዘንግቼዋለሁ።ከዚያ ያን የተረገመ ክፍል ዘወር ዘወር ብዬ ቃኘሁት።

በመጨረሻ ሐኪሙን ፈቱትና ሁለት ሰዎች ተሸክመው አወጡት።በአጠገቤ ይዘውት ሲያልፉ የተላላጡትንና ያባበጡትን እግሮቹን አየኋቸው። ቀጠለና ደህንነቱ እኔን ጠራኝ።ጠጋ ብዬ እፊቱ ስቆም፣ ,እውነቱን ትነግሪኛለሽ፣ ወይስ ያየሽውን ዘዴ እንጠቀም?` ብሎ አፈጠጠብኝ።

,በጽሁፌ እውነቱን ተናግሬያለሁ፣' አልኩ፣ ረጋ ብዬ። ለካድሬው ምልክት ሰጠው።ከመቅጽበት ዓይን እግሮቼ በገመድ ተጠፍረው፣ ተዘቅዝቄ ተሰቀልኩ።የኔንም ዓይኖች ሸፈኗቸው።የሐኪሙን አፍ የለጎሙበትን ቡትቶ በኔም አፍ ውስጥ ወተፉት።ሐኪሙን የጠበጠበው ካድሬ እኔንም በቢጫ ጎማ ጨፈጨፈኝ። አልፎ አልፎ ድብደባውን ገታ ሲያደርግ፣ የደህንነት አባሉ ቡትቶውን ከአፌ አውጥቶ እውነቷን እንዳወጣ ያዘኛል።የማውቀውን ሁሉ በጽሁፌ ገልጫለሁ ስለው አፌን መልሶ ይወትፋል፣ ካድሬው መጠብጠቡን ይቀጥላል።

ስቃዬ ከሁሉም የሚከፋው የደህንነት አባሉ ጉሮሮዬን በእጁ በሚያፍነው ጊዜ ነበር። ነፍሴ ሲጥ ብላ የወጣች ሲመስለኝ ለቀቅ ያደርገኝና እውነቱን እንዳወጣ ያዘኛል።በቃሌ ጸናሁ።በመጨረሻ እኔን ከዚያ ሲያወጡኝ፣ የሐኪሙ ሚስት መስከረም ተጠርታ ገባች።

ተገርፈን የወጣነው ደግሞ በባዶ እግራችን በስሚንቶው ላይ እንድንሄድ ተደረግን።በሕይወቴ ስቃይ በዚያ ደረጃ ቀምሼ አላውቅም።ጠመንጃ

ያነገቱ ጥቂት ወታደሮች በዙሪያችን እየተንጎራደዱ እንዳንቆም ይከታተሉናል።ስቃዩ ከመጠን በላይ ቢጠናብኝ፣ ትንሽ ተንፈስ ልበል ብዬ ቁጢጥ አልኩ።'ቀጥይ' አለ ደግሞ ሌላ ሰው።ሳላስበው ቀኝ ጉንጩ በጥፊ ተናጋ።ሌላ አብዮት ጠባቂ መስሎኛል።ያው ጠና ያለው የደህንነት አባል ነው። ከምኑ ውስጥ እንደወጣ እግዜር ይወቀው። ይህ ሰው በርግጥም ይጠላኛል።"(270)ስትል ደምድማለች። በመጨረሻም ወደታሰሩበት እንዲመለሱ ተደርገዋል።

በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ማርክሲዝምን ትክክል አይደለም፣ አይሰራም ብሎ ማለት የማንም መብት ነው።ከአንድ ፓርቲ የመውጣጥና የመግባት መብትም የግለሰቡ ነው።ጸሃፊዋም ከኢሕአፓ አባልነት የመውጣት መብት እንደማገኛውም ሰው አላት።

## ከፓርቲው መውጣትና የወሰደችው አቅዋም፣

„የሸሸሁትም ፓርቲው ስህተት ሰለሰራ ሳይሆን፣ እንደዚያ ያሉ የቡድን ስብስቦች አባላታቸውን ጭፍን ተከታዮቻቸው በማድረጋቸው ነበር።በተጨማሪም ከነሱ ወጣ ያለ እምነት ባላቸው አባላት ላይ ከፍተኛ ጥላቻ የሚያስርጹ መሆናቸው አስጠላኝ።"(304) የሚለው አባባል ላይ እንዲህ ማለት እፈልጋለሁ። ጭፍን ተከታይ አንድ ሰው ሲሆን ነገሮችን ሳይገነዘብ ዝምብሎ የሚያጨበጭብ ሰው ነው። የዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ጭፍን ተከታዮች ማለት ይቻላል። ፓርቲው ግን ጭፍን ተከታዮች ሳይሆን የሚፈልገው ነገሮችን በበለጠ ተገንዝበው የድርጅቱን ዓላማዎች ተግባራዊ የሚያደርጉና ስህተቶች የሚሏቸውንም ሲጠቁሙ ነው።ፓርቲው ጭፍን ተከታዮች ለማድረግ የተንቀሳቀሰበት ሁኔታ መኖሩን መቀበል ይቸግረኛል።"በተጨማሪ ከነሱ ወጣ ያለ" የሚለው አገላለጽ ጸሃፊዋ በአንድ ወገን፣ እነርሱ በሌላ ወገን ሆነው እንደሆኑ ነው።ይሄ ጅምላ ፍረጃ ጥሩ አይመስለኝም። ጸሃፊዋ እንዳላቸው ሌላ ሃሳብ ስላላቸው ጥላቻ ያደረባቸው አባላት ሊኖሩ እንደሚችሉና ጥላቻም የማያድርባቸው አባላት ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ ያሻል።

„የምንሰራው ስራ የሰውን ሕይውት በማጥፋት የሚፈጸም ከሆነ፣ ጥሩነታችን እምኑ ላይ ነው? ከሚገባው በላይ መጎዳዳትና ደም መፋሰስ አይቻለሁ። ሃይል የሚለው ቃል ራሱ ጥላቻን ቀሰቀሰብኝ። የከተማም ሆነ የገጠር የትጥቅ ትግል ሁለቱም ደም መፋሰስንና በጉልበት መጠቀምን ስለሚያመጡ፣ ሁለቱንም ተቃወምኳቸው።'የለውጥ ሁሉ ቁንጮ ዋጋው የሰው ሕይወት ሊሆን ይገባል።ማናቸውም ለውጥ በሰላማዊ መንገድ ነው መምጣት ያለበት' የሚል ቁርጠኛ አቋም ወሰድኩ።"(305)በማለት ጸሃፊዋ ገልጻለች።ስለዚህ አማራጩ የጦር መሳሪያ የማይመረትባት ዓለምንና ሰው ሌላውን ሰው የማይገድልበት ዓለም ነው። ይሄ ግን ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ ተግባራዊ ሆኖ አልተገኘም።ይሄ ካፒታሊዝም አይዲዮሎጂም የሚንቀሳቅሰው ሃይልን በመጠቀም፣ ሌሎች ሰዎችን በመግደል እንደሆነ ጸሃይ የሞቀው እውነት ነው።ስለዚህ ጸሐፊዋ ለዓለም ሕዝቦች ያለመችው ሕልም ካለ ብታካፍለን መልካም ነው። እንዲያውም የዓለምን ሕዝቦች ወደ አንድ ሚሊያርድ ለመቀነስ በጦርነት፣ መሃን በማድረግ፣ በክትባቶች፣ በረሃብ፣. . . ወዘተ የካፒታሊስቱ የምዕራቡ ዓለም የታወቁ ሃብታሞች ተግባራዊ እያደረጉ ናቸው። ስለሆነም ሕይወት ሌላ እስካሁን ያልታየ ነገር ታይቷት ከሆነ ታካፍለን።

„የስዕልና ሙዚቃ ታሪክን ካነበብኩ በኋላ፣ ,በልዩ የአእምሮ ችሎታቸውና በህልማቸውም አማካይነት ዓለምን ወደተሻለ ደረጃ የሚያደርሷት ግለሰቦች ናቸው።' ብዬ ደምድሜያለሁ።ይህ መሬት አንቀጥቅጥ ግኝት ላይሆን ይችላል።ለኔ ግን በጊዜው ስለዓለም አዲስ አተያይ ሰጠኝ።ይህን ወደመሰለ ድምዳሜ ከደረስኩ ዘንዳ፣ ,ልቦናዬን ሲኮረኩረው የነበረው ለውጥ የሚመጣው በተደራጀና በተቀናጀ ጥረት ብቻ ነው' የሚለውን እምነት አውልቄ ልጥለው ቻልኩ።"(364)

ይህ አባባል በእኔ ግንዛቤ የአይዲዮሎጂ ትርጉም ያለው ይመስላል። ፕራይቬት ኦነርሽፕ ከሚለው የኒዎ ሊበራል አይዲዮሎጂ ጋር ለመጠጋጋት እንደሆነ ነው የተረዳሁት።ይህንን አቅዋም መውሰዱ

መብት ነው። ሁልግዜ ዓለምን ወደተሻለ ደረጃ የሚያደርሷት የግለሰቦች ስብስብ ናቸው። መደራጀትና መቀናጀት ግን ግድ ነው። ያለበለዚያ ግለስብ እቤቱ ቀሪ ነው።ከሌሎች ጋር አብሮ መቀናጀትና መደራጀት የሚፈለገውን ነገር በተሻለ ሁኔታ እውን ለማድረግ ያስችላል።

„ተምኔታዊ ዓለም ለመፍጠር ከመፍጨርጨር ይልቅ የግል ሃላፊነት፣ የግል ሉዓላዊነትና ሃቀኝነት አብዝቶ የተሻለ መሆኑን ተገነዘብኩ።“(376) „የግል ነጻነት“ የምትለዋ በአይዶዮሎጂ መልክ ከሆነ ያው ኒዎ ሊበራል አይዲዮሎጂ ተከታይነትን የሚያንጸባርቅ ነው።ተምኔታዊ ዓለም የሚለውም ወደ ሌላ አይዲዮሎጂ ለመንደርደር የተሰነዘረ ካልሆነ የግራው አይዲዮሎጂ ነበረ፣ ዛሬም አለ፣ ነገም ይኖራል።ስለሆነም ተምኔታዊ አይደለም።

በመጨረሻም ሕይወትን ይህንን መጽሐፍ በመጻፏና ለአንባቢያ በማቅረቧ ከልብ አመሰግናለሁ።

ከተንሳይት በቃና

ማርች 3 ቀን 2016 ዓ.ም.